# ትንቢት ምንድነው(21)

## ከተለያዩ ክፍሎች የተውጣጣ

የጥናት ዓላማ፡- የተለያዩ የመጽሐፍ ቅዱስ ክፍሎቸን በመመልከት ስለ ትንቢት ሊኖረን ባለን አመለካከት ላይ የበለጠ እውቀትን ለመቅስም፡፡

የምናሰላስለው ጥቅስ፡ ‹‹ሕዝቤ እውቀት ከማጣቱ የተነሳ ጠፍቶአል፡፡ እውቀትን ስለናቃችሁ እኒም ካህናት እንዳትሆኑ ናቅኋችሁ፡፡›› ሆሲዕ 4፡6

1. **1ኛ ተሰ 5፡19-22** ከዚህ ክፍል ትንቢትን በተመለከተ መረዳት የሚኖርብን ነገሮች ምን ምንድናቸው? እንዴት ነው ትንቢት የሚመረመረው? ምሳሌ በመስጠት አስረዳ፡፡
2. **1ኛ ጢሞ 1፡18** እና የሃዋ ሥራ **21፡10-11** በማንበብ አንድ ልናረጋግጥ የምንችለው እውነት ምንድነው ትላለህ?
3. **ዘዳ 18፡22** ትንቢት ከእግዚአብሄር ለመሆኑና ላለመሆኑ የሚሰጠን መመዘኛ ምንድነው?
4. **ዘዳ 13፡1-5** ሀሰተኛ ነብይ አንዳንዴ ትንቢቱ ሊፈጸምለት እንደሚችል ያሳየናል፡፡ ይህ ክፍል ታዲያ ለምንድነው ነብዩን አትስሙት የሚለን? ሀሰተኛ ነብይ ከሆነ ታዲያ ለምን ትንቢቱ ይፈጸማል?
5. ኤር 23፡25-29 ነብይ ትንቢቱን መናገር ስለሚኖርበት ሁኔት ምን ያስተምረናል? እውነተኛ ትንቢትንና ሀሰተኛ ትንቢትን ለመለያ የተነገረ ነገር በዚህ ክፍል ምንድነው?
6. ኤር 28፡7-11 ሀሰተኛ ትንቢት በተለይም ደግሞ ከእግዚአብሄር ቃል የሚቃረን ትንቢት የሚናገርን ሰው ምን ማድረግ እንደሚገባ ነው ከዚሀ ክፍል የምናየው?
7. ኢሳ 30፡9-11 በዚህ ክፍል ላይ ያሉት ሰዎች ከነብያቶቻቸው የሚጠይቁት/የሚፈልጉት አይነት ትንቢት ምን አይነት ነው? ለምንድነው የዚህ አይነቱን ነገር የፈለጉበት ምክንያት?